# "ገለልተኛ"

*(አገር ያፈራውን ሕዝብ ያበረከተውን የምግብ ዓይነት ሁሉ፥ ከሕብ ጋራ በመሻማት ላይ እያለን፥ በመከራ ጊዜ ከሕዝቡ ራስን ገለልተኛ ማድረግ እራስን ከግምት ላይ መጣልና፥ ከተፈጥሮ ውጭ ማድረግ ነው::)*


**ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ**
nigatuasteraye@yahoo.com


ጥቅምት ፬ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.

ሰው የሆነ ሰው እንኳን በሕይወቱ ሞቶም ከሕብረተ ሰቡ ገለልተኛ አይደለም:: እግዚአብሔርም እንኳን ገለልተኛ አይደለም:: በዋሻ የዘጉም ባሕታውያን አይደሉም:: እውነቱና ጽድቁ ይህ ሆኖ ሳለ ሃይማኖት ሲፋለስ፥ ዝብ ሲጎዳ ገለለተኛ ነኝ የሚል ካህን ወዮለት!

ገለልተኛነትን በማንኛውም አንጻር ብንመለከተው ከፈጣሪና ከተፈጥሮ ሕግ ውጭ ነው:: በሃይማኖታችን አንጻር ብናየው በመለኮትና በሰው መካል ያለው የባሕርይ ልዩነት የማይቀራረብ ሲሆን፥ እግዚአብሔር ሰውን ከወደቀበት ዘላለማዊ ጥፋት ያወጣው፥ በመዋሐድ እንጅ ገለልተኛ ሆኖ አይደለም::

የኦርቶዶክሳውያን ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት "አማኑኤል" ከተባለበት በመነሳት፥ "ክርስቶስ ፍጡር፥ ኢፍጡር ውእቱ፥ ዘሰ ንቤ ፍጡር: በእንተ ዘተሳተፈ ሥጋ ድካመነ" እያሉ ያስተምራሉ:: ማለትም:-ክርስቶስ በመለኮቱ ፈጣሪ ነው:: ይሁን እንጅ፥ ከኛ ጋራ የተወሐደበት ደካማው ሥጋችን እራሱ የፈጠረው ፍጡር ነው":: ሚችና ተፈጣሪ የሆነውን ሰው ለማዳን፥ ፈጣሪና ሕያው የሆነው አምላክ "ቃል ሥጋ ሆነ":: መለኮታዊ ባሕርዩን አካሉን ከፈጠረው ከኛ አካል ጋር በማሐድ አዳነን:: ባጭሩ "እግዚአብሔር ከኛ ጋራ ሆነ"፥ ተወሐደ ማለት ነው::

ወደ ሰው ስንመጣ በእስታሊን ጊዜ የነበረው ራሽያዊው ጴጥሮስ የተናገረውን ከዚህ ላይ ብጠቅሰው፥ እነ አቡነ ጳውሎስ በገለልተኛነት የቆልፉትን የባይታወርነት ስሜት ሰብሮ ወደ ዓይነ ሕሊናችን በመግባት የርሕራሄና የሰባዊ ስሜት ብርሃን እንደሚፈነጥቅብን አልጠራጠርም::

ይህ ሰው በእስታሊን ዘመን ተሰዶ ወደ እንግሊዝ አገር ሄደ:: የወገኑን ሁኔታ በሩቂ እየሰማ ያዝን ነበር:: በእንግሊዝ አገር ያፈራቸው ጓደኞቹ "እንደንስ እንብላ እንጠጣ" ይሉታል:: ከሐዘንና ከመተከዝ በቀር ግብዣቸውን አይቀበልም ነበርና፥ "ምን ያሳዝንሐል? እያሉ ይጠይቁትም ነበር:: "በሩቂ የምሰማው የወገኔን ሥቃይና ችግር ውስጤን እየጠበሰኝ ነው" ይላቸው ነበር:: እነሱም መልሰው "አንተ ወደዚህ የመጣኸው ከዚህ ለመላቀቅ ነው" ይሉታል:: እሱም ይመልስና "ከተወልድኳባት ከራሻያ እንግሊዝ አገር ቀርብ ናት:: የሚለያት ባሕር ነው:: ከዚህች ምድር እርቄ በሌላ ፕላኔት ብኖር፥ የሰው ሥጋ ጥብስ ሱስ ያሰከረው መንግሥት የሚጠብሰው የወገኔ ሥጋ ጢሱ እዚህ ድረስ እየመጣ ያፍነኛል::" ይላቸው ነበር:: ይህ አነጋገር ለመንፈሳውያን ሰዎች ብቻ አይደለም፥ ሰው ለሆነ ሁሉ ሰው ምሳሌነቱ ሊሻር የማይችል በአዕምሮ ተቀርጾ መኖር ያለበት ሕያው የሞራል ሐውልት ነው::

በቤተ ክርስቲያናችን ገለልተኛ ማለት፥ መነኩሴ ወይም ባሕታዊ ማለት ነው:: የብሕትውናንና የምንኩስናን ተግባር አሁን በጊዜያችን ከሚካሔደው ጋራ ስናስተያየው ፈጽሞ ይጋጫል:: የባሕታውያንና የመነኮሳት ምሳሌ ምሳሌ ሆኖ የሚጠቀሰው አባ እንጦንስ ነውና፥ ያደረገውን እንመለከታለን::

የእንጦንስ ዘመን እኛ አሁን እንዳለንበት ክፉ ዘመን ሆነና ሕዝቡ በመሪዎቹ ተሠቃየ:: ታሪኩ

"*Antoni decided to break his solitude, and return to Alexandria in order to be near the people in their dire distress. He also desired exceedingly to be among the people . . . . Went to the Hall of Judgment, and stood opposite the wicked judge who had issued this decree. Antoni declared in a thunderous voice before him that he would never forsake his children, but would stand by them to the very end." (The story of the Copts, page 61)* ይላል:: ማለትም አባ እንጦስ ከሕዝቡ ጋራ ለመሰለፍ ወሰነ:: የዚጋበትን ዋሻ ሰብሮ ወጣ:: በገዳም ያሉትን ማኀበረ መነኮሳትን ደቅድቆ በጭንቅና በመከራ ተይዞ በመቃተት ላይ ወዳለው ሕብረተ ሰብ ገሠገሠ:: ባስጨናቂው ዳኛ ላይ እንደመብረቅ ጮኸ:: እስከ መጨረሻ ከመንፈስ ልጆቼ ጋራ እቆማለሁ:: አልለያቸውም እያለ ጮኸ::

በብሕትውና ከሕዝብ የተገለሉ፥ በምናኔ በገዳም የሚኖሩ አባቶች የሚገለሉት ከሥጋዊ ነገር ነው:: በሕሊናቸው ለሰከንድ እንኳ ከሕብረተ ሰቡ አይገለሉም:: ከሕዝብ ላለመገለል አስደናቂ ሥርአት አላቸው:: በአራቱ ማእዘናት ሰፍሮ ከሚኖረው ሕዝብ የሚአገናኟቸው ልኡካን አሏቸው:: የነዚህ ልኡካን አገልግሎት ገዳሙን ወክለው በዓለም የሚኖሩትን መጎብኘትና መርዳት ነው::

በሚአደርጉት መንፈሳዊ ጉብኝታቸው: በድንበርም በሌላም ሰው በተጣላበት፥ ባልና ሚስት ተጋጭተው የተቀደሰው ትዳር ሲፈርስ በደረሰበት መንደር ድንገት ይደርሱና ያስታርቃሉ:: ወረርሽኝ በሽታ ገብቶ ርዳታ የሚአስፈልገው ገመምተኛ ብቻውን ሲጥር ያገኙታል፥ ገላውን ልብሱን አጥበው፥ ቤቱን ጠርገው ውሀ አጠጥተው ማታ ወደገዳማቸው ተመልሰው በገዳሙ ላሉ አባቶች የገጠማቸውን ሁሉ ይገልጻሉ:: ገዳማውያን አበው ከሰሙ በኋላ "ወበከመ አቀብከን እምነግሕ እስከ ሠርክ እቀበን እግዚኦ እምሰርክ እስከነግህ" ማለትም:- "ከጧት እስከዚህች ሰአት ያቆየኸን አምላካችን ሆይ! እንደገና ከዚህች ከደረስንባት ምሽት እስከነገ ጧት ጠብቀን ከዚህ የተሻለ እንጅ የባሰ አታሰማን" የሚለውን ይጸልያሉ:: ይህ ጸሎት ከልኡካኑ ስለሰሙት ስለ ኅብረተ ሰቡ እንጅ ስለ ለራሳቸው አይደለም:: ከኅብረተ ሰቡ አልተገለሉም ማለት ነው::

ጦርነት ሌላም መቅሰፍት ሲመጣ እስኪበርድ ድረስ በሰው ቤት ሳይገቡ በየደረሱበት ደብር መቃብር ቤት እያደሩ ሕጻናት በሚጫወቱበት፥ ጥጆች በሚፈነጩበት መስክ የመንደሩን ሕዝብ እየሰበሰቡ፥ ቃጭል እያቃጨሉ ሕዝቡን በእግዚኦታ ማታ ማታ እግዚኦታን ይመሩ ነበር:: ከዓለሙ ጥቅም እራሳቸውን ያገለሉ፥ ከመከራው ከጭንቁና ከስቃዩ ግን ከመጋራት አልፈው ከሕዝቡ አስቀድመው የሚቀምሱት እነሱ ነበሩ::

ሰው የትም ይሁን፥ ምንም ይሁን፥ የኅብረተ ሰብ አካል ነው:: አገርም የእትብቱ ቤት ነው:: እራሱን ከቤቱ የሚአገለው ቤቱ ሲቃጠል ከእሳቱ ለማምለጥ በሚወስደው ርምጃ ነው:: "ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይረዳም" እንዲሉ፥ ቤት በእሳት ሲያዝ ከቤት ሮጦ የሚወጣው ለገለልተኛነት ነፍሱን ለማትረፍ ብቻ አይደለም:: እየጮኸ አፍርና ውሐ በመርጨት እሳቱን ለማጥፋት ነው:: በጩኸቱ የጎረቤት እርዳታ ለማግኘትም ጭምር ነው:: ይህን የማያደርገ ከሆነ፥ ለቤቱ ደንታ የሌለው የራሱን የቤት ጣሪያ እያነደደ የሚሞቅ ለገዛ ቤቱ ባለጋራ ጣላት ነው::

ወደ ቋንቋችን ስመለስ፥ "ጋራ" የምንላት አገባብ፥ የምታጋራው የሚፋቀሩትን ወገኖችና ወዳጆች ብቻ ሳይሆን፥ በጠላትነት የሚተያዩትን ጭምር ነው:: በግድያ የሚፈላለጉ ሰዎች ባለ "ጋራ" ናቸው ይባላል:: ይህች ቃል ማኀበራዊ ግንዛቤያችንን በውስጠ ወይራነት የምትገልጽ ናት:: "ባለ ጋራ" ማለትም አንዱ ከሌላው በክፉም ሆነ በደግ የሚአጋራው ጉዳይ አለው ማለት ነው:: በሌላ በኩል "ባለ አንገጣ" ም ይባላል:: ይህ የሚያመለክተው ሰው በተቃራኒውም ሆነ በተስማሚው ካንተ የምፈልገው ነገር አለኝና መልስልኝ ስጠኝ: አምጣልኝ ማለት ነው::

ይህን የተመለከቱ Mbiti የተባሉ አፍሪቃዊ ሊቅ ስለ አፍሪካ ባሕል በጻፉት *"He owes his existence to other people, including those of past generations and his contemporaries. He is simply part of the whole. The communiity must therfore make, creat or produce the individual; for the individual depends on the group."(page 108)* ብለዋል:: ማለትም:- ሰው የሚኖረው ለሌሎች ሰዎች ነው:: ላለፉት ላሉትና ወደፊትም ለሚመጡት ነው:: አንድ ሰው የጠቅላላው ሕብረተ ሰብ አካል ነው:: ስለዚህ ኅብረተ ሰብ ነጠላ ሰው ያስገኛል:: ነጠላው ሰው ደግሞ በጠቅላላው ኅብረተ ሰብ ውስጥ ሕልው ነው አሉ::

ያፍሪካ በተለይም ተጠብቆ የቆየው የኛ ማኅበራዊ ትስስር ለተፈጥሮ እጅግ የቀረበ ነው:: ከተፈጥሮ ያየሁት ብጠቅሰው አንባቢን ማስቸልት አይሁንብኝና፥ ሰው ይቅርና እንስሳትም ከበረት ተካፋይ ወገናቸው አንዱብሞት ከተለያቸው፥ ውለው ከውጭ ሲመጡ ደሙ ታጥቦ ካልቆያቸው በቀር፥ የወገናቸው ደም በፈሰሰበት መሬት ላይ ጥጆች ሳይቀሩ አፍንጫቸውን ተክለው ይንጫጫሉ:: ሥጋውን የተቀራመተውን ሰው ሁሉ አፈር በበላሁ እያሰኙ ሲአስለቅሱት አይቻለሁ::

አንዳንዶቹ ተደብድበው ወደበረት እንዲገቡ ሲገደዱ፥ ወደ ውጭ በመፈርጠጥ የሚሸፍቱ የሚገለሉም አሉ:: በዚህ መልክ የተገለለ ከብት እስኪረሳው ድረስ ሳር አይበላም::ይህ አይነት መገለል ከባሕርይ ውጭ ጎጅ የሆኑ ነገሮች ሲፈጠሩ የጉዳት ሸክም ካቅም በላይ ሲሆን
የተፈጥሮ ባሕር መሆኑ ነው::

"አንበሳ በጫካ ዝንጀሮ በገደል፥
ወተት ይሸፍታል እንኳን ሰው ሲበደል"

እያለ የአገራችን ሕዝብ የሚአንጎራጉረው፥ መሸፈት ተጽእኖ የሚአስከትለው ግዴታ እንደሆነ ያመለክታል:: ሽፍታ ሲሸፍት ከመንደሩ ገለል ይላል:: የሚፋለመው ባላጋራ በሱ ላይ የወረወረው አካባቢውን እንዳይጎዳበት፥ አካሉን ብቻ ገለል አደረገ እንጅ መንፈሱ ስሜቱ ከሕዝቡ የተለየ አይደለም:: የእውነተኛ ዜጎች በተለይም የመንፈሳውያን ሰዎች ስደት ከዚህ የሚርቅ አይመስለኝም:: የዚህ ተቃራኒ ወንበዴ ነው::

ወንበዴ ከሽፍትነት ፈጽሞ የተለየ ነው:: ለወገን ደንታ የሌለው፥ መንፈሱን ሞራሉን ከሕዝብ ያገለለ፥ አካሉን በሕዝብ ሰውሮ በሱ ላይ ለሚደርስበት ሁሉ ችግር ሕዝቡን ሽፋን አርጎ፥ የሕዝቡን ቁስል መከራና ሥቃይ ወደራሱ ጥቅም ገልብጦ፥ ለስሞታ የሚአቀርብ፥ ወንድም ከወንድሙ፥ ወገን ከወገኑ እንዲአገል የሚያወናብድ አካል ነው::

ሰውን ከወገኑ ያገላል የሚባለው የመጨረሻው ነፍስን ከሥጋ ለይቶ ሬሳ የሚአደርገው ሞት ነው:: ሞትም እንኳ ቢሆን፥ ኢትዮጵያውያን እናትና አባቶች የወለዱት ልጅ ሞራለ ቢስ አሳፋሪ ሲሆኖ በቁሙ ሞቶ ሲአሳፍራቸው አጥንቴ እሾህ ሆኖ ይውጋህ! በመቃብሬ አትቁም! ይላሉ:: ይህ አባባል በወረስነው ሃይማኖት፥ ሞራልና ታሪክ አማካይነት ካለፈው ትውልድ ጋር ያለንን ትስስር ያሳያል::

አንዳንድ ሰዎች: ያገራችን ሰው ተራብ: ተበደለ እያሉ ከወገንም ከውጩም ገንዘብ ይለምናሉ:: ከባለአምጣነትና ከባለ ጋራነት ስሜት በራቀና በወገናዊነት ርኅራሄ ላይ ብቻ በተመሰረተ ግንዛቤ ከሆነ ነገሩ ባልከፋ ነበር:: ነገር ግን የጉዳቱን መንስኤ ሳይጠቁሙ፥ ችግር ፈጻሚውን ሳይገስጹ፥ ምስክርነታቸውን ከሕዝብ ሰርቀው ገንዘብ ሰብስቡ ብቻ የሚሉ ከሆነ፡ ስለምትተርፋቸው ቅንጥብጣቢ ሲሉ አደረጉት እንጅ፥ ከ ባለ ጋራ ነት (ከ ባለአምጣነት) ገለልተኛ ናቸው አያሰኛቸውም:: ይልቁንም የሕዝቡን ቁስል መለመኛ በማድረግ ለበለጠ ዘላቂ ጉዳት መሸጋገሪያ ድልድይ ለማድረግና፥ ለሚጋሩት የሳንቲም እንፍርፋሪ ሲሉ ነው ቢባል ሊአስተባብሉ አይችሉም::

በደህና ዘመን፥ ከሃይማኖትና ከሰባዊ ስሜት ራሳቸውን አግልለው በልብሳቸው በንግግራቸው ተሸፍነው ወደ ህዝቡና ወደ ቤተ መቅደሱ የሚመጡ ካህናት በጣም ጥቂቶች ነበሩ:: አብዛኛው ሕዝብ አስቀድሶ ወደየቤቱ ከመሄድ በቀር የካህናቱን ዝቅጠት ለይቶ ለማወቅ እድል አልነበረው:: የካህናቱን ብቃትና ሞራል የለሸነት ሚረዱት ምዕመናን ቁጥራቸው ትንሽ ነበረ:: በካህናቱ አታላይነት ያዝኑ የነበሩ ሊቃውንት "በቅኔና በቅዱሳት መጻሕፍት ያልታሸ ሰው ወደ ቤተ መቅደስ ከገባ ወደ ትኋን ይለወጣልና፥ ትኋን እንዳትሆኑ ዘልቃችሁ ተማሩ" ይሉ ነበር::

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሰው ትኋን ተብሎ ሲሰደብ፥ በክርፋቷና በደም መጣችነቷ የሰውን ባሕርይ ለመግለጽ ብቻ ይመስለኝ ነበር:: ለካ ከዚያ የራቀ አስቀያሚና አጸያፊ ተግባር አላት:: ዛሬ ከኔ ጀምሮ የካህናቱን ጠባይ ስረዳ፥ ቱሐኗን እየጠቀሱ የሚገስጹ አባቶች ምንኛ አስተዋዮች እንደነበሩ እጅግ ያስደንቀኛል::

የፍጥረት ተመራማሪ ጠበብቶች እንደሚአስተምሩን፥ ቱሐን የሰው ደም ለመምጠጥ ሁለት ተራዛሚ ቀንዶች አሏት፥ አንዱ በሰው አካል ላይ በመትከል የምትመጠውን ደም የሚያላላ ኬሚካል የምትረጭበት ነው:: ሌላው ቀንዷ (አንቴናዋ) የላላውን ደም የምትመጥበት መሳሪዋ ነው::

የዚህ ዘመን ካህናት እንደተኋና ሁለት ተራዛሚ ቀንዶች አሉን:: አንደኛው የሕዝቡን መንፈስ የሚያላላና የሚአዘናጋ ሳይገባንና ውስጡን ሳንረዳ የምንቀድሰው ቅዳሴ ነው:: ሌላው ቀንዳችን ከሕዝቡ ገንዘብ የምንመጥበት ዘዴ ነው:: በዚህ ዘመን ያለን ካህናት የማናካሄደው ዘረፋ ከመጠን በላይ በዝቶ፥ ወደቱሐንነት የተለወጥን በመሆናችን፥ ቱሐንነታችን ለሁሉም ግልጽና ይፋ ነው:: አብዛኛው ምእመናን የኛን ደባ ለይቶ ለማወቅ እንደወትሮው ችግር ይገጥመዋል ብየ አልገምትም::

የአምላክን ቃል የሚመሰክር ካህን ይቅርና፥ በዓለም የሚኖር ሰው የሚመርጠው ጓደኛና ወዳጅ እንደ ባለሁለት ቀንዷ ቱሐን የሕዝብ ገንዘብ የሚመጥ መሆን የለበትም:: ኀብረተ ሰብ በችግር ላይ ሲወድቅ፥ ሃይማኖቱ ሲናጋ ገለልተኛ ነኝ የሚለውን ካህን፥በሌላም በብዙ ምሳሌዎች ሊገለጽ ትችላል:: ሰሎሞን የተነቃነቀ ጥርስ ነው ብሎታል:: ምሳ ፳፮:፲፱) የተነቃነቀ ጥርስ ካልወለቀ፥ ለማላመጥ የማያስችል የራስ ምታት በሽታ፥ ለሌላው ሁሉ ጥርስ መናድን የሚአስከትል እንደሆነ ሁሉ፥ የማይረባ ካህን ሆነ ጓደኛ ለተቀደሰ ዓላማና ግብ እንቅፋት ነው::

"ካይረባ ጓደኛ ይሻለኛል አባይ፥ ይሻላል ተከዜ፥
በየት እንሻገር ያሰኛል በጊዜ"

እያለ እንደ ብርቱካን ያለችውን የዘመናችን ጀግና ያፈራ ሕዝባችን ያስተማረንን ልንረሳው አይገባንም:: ገለልተኛነት፥ የሕይወት መስዋእትነት ከሚያስከፍለው መከራ ራስን ደብቆድ፥ ርካሽ ለሆነ ለጥቅም ባላጋራ ሆኖ መገኘት አሳፋሪና ውርደት ነው:: ይህን የተረዳች ኢትዮጵያዊቷ ብርቱካን ለአሳሪወቿ የውርደታቸው፥ ለኢትዮጵያ ግን የክብራቸው ባለጋራ (ተካፋይ) ለመሆን በቅታለች::

ተልእኮውን የሳተ ካህን ባልትና የሚአጥራት ሴት የሰራችው የኀጎለ ሽሮ ነው:: የኀጎለ ሽሮ ቢጎርሱት ባፍ ላይ ዱቄት እየሆነ ለመዋጥ ያስቸግራል:: አላማና ወሳኝ መንፈስ ከሌለው ጓደኛም ይሁን ካህን ጋራ መሰለፍ፥ መካከል ላይ ሲደርስ "የናቴ መቀነት ጠለፈኝ" በማለት ገለል ይላል:: ተጸይፎ የተፋውን ሊጥ ከሚልሱት ጋር ዞሮ በመግጠም መላስ ይጀምራል:: በአላማው ጸንቶ የቆመውን ወንድሙን ወደ አመድነት ለመለወጥ፥ የራሱን የራሱን ዱቄታማ መንፈስ በላው ላይ ይረጭበታል::" ይላሉ አባቶች::

ለመሆኑ አንድን ሰው ከወገኑ ወይም ከቤተ ክርስቲያኑ ገለልተኛ የሚያደርገው ምንድነው? ለሃይማኖቱ ለወገኑ መመስከሩ ነው? በሕዝቡ ጭቅላት ላይ ተቀምጠው የሚቀልዱትን ትክክል አይደላችሁም ማለቱ ነው? ለሕዝብ "ባላ ጋራ: ባለ አምጣ" አለመሆን ነው? እነሱ ከሚዘርፉት ከቆሳቁሳዊ ጥቅሙ ተከፋይ አለመሆኑ ነው? የገለልተኝነት መስፈርት ሕዝቡን ከማስረገጥና ከማስደ ብደብ ርቆ መገኘት ከሆነና ሁሉም ተስማምቶ ከተቀበለው፥ የተቀበለውን ሕዝብ አብዷል ከማለት በቀር ሌላ ምን ቋንቋ አለ?

ነቢዩ ኤርምያስ አንዲት አረፍተ ነገር ተናግሮ ያቀረበው ጥያቄ በዚህ ዘመን ያለነውን ካህናት ነን የምንለውን ብቻ አይደለም፥ ማነኛውንም ነፍስ ያለውን ሰው ሁሉ እንቅልፍ እንደሚነሳ ይሰማኛል:: "በፍጻሜውስ ምን ታደርጋላችሁ? (ኤር ፭:፴፩:)" ብሎ ካቀረበው ጥያቄ በፊት የተናገረውን እጠቅሳለሁ:: "የምታስደንቅና የምታስደነግጥ ነገር በምድር ላይ ትሆናለች፥ ነብያት ሐሰት ይናገራሉ:: የካሕናት መንፈስም በሐሰት መንፈስ መመራት ይጀምራል:: ሕዝቡም እንዲህ ያለውን ወዶ ይቀበላል" አለ::

ነቢዩ እንዳለው እውነትን በመናገር ምሳሌ መሆን የሚገባው ታላቁ ካህን ከዋሸ፥ ካህኑ ሰባኪው ሁሉ በዚህ መንፈስ ከተመረዘ፥ ሕዝቡም ወዶ ከተቀበለ "የምታስደንቅና የምታስደነግጥ ነገር በምድር ላይ ትሆናለች" ያለውን በማስታወስ 'አያስችልም እንጅ የሚአስችል ከሆነ' እራስን ከሁሉም ከማግለል በቀር ሌላ ምን አማራጭ ይኖራል?

በዚህች ታሪካዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካህናት ነን የምትሉ ሁሉ ካህናት ወገኖቼ! መገለል ያለብን በሕዝቡ ላይ የመከራ ድንጋይ ከሚከቡት ሰዎች ኅብረት ነው:: ለተዋሕዶው ሃይማኖት ጠባቂና ዋቢ ያጣበት ዘመን መሆኑን በመረዳት፥ ከየትም እየለቃቀሙ የክሕደት መጽሐፍ እያሳተሙ በመቸርቸር ህዝቡን ከሚዘርፉና የተወህዶን መሠረተ ሃይማኖትን ነቃቅለው ለመጣል ጥረት ከሚያደርጉት ሰብሮ ገቦች ነው::

ከአገርና ከወገን ተለይተን መሰደዳችን፥ በያለንበት ሆነን በወገን ላይ እየነደደ ያለውን እሳት በውሐ በአፈር በምንችለው አቅም ሁሉ ለማጥፋት መሆን ነበረበት:: በአከባቢያችን አላፊውንም አግዳሚውንም ሁሉ ለማሰማት ነበር:: በዜግነትና በቋንቋ የማይዛመደን ባእድ ሲጮህ፥ እኛ ግን በአቡነ ጳውሎስ አፍዛዥ ስብከት ገለልተኞች ነን በማለት አፋችንን ዘጋን:: እኛ ተዋረድን ከግምት ላይም ወደቅን እንጂ፥ በውስጥም በውጭም ያለው ሁሉ ኢትዮጵያዊ እስካሁን ያለኛ ኅብረት መከራውን ተወጥቶታል:: ወደፊትም ይወጠዋል::

ወዮ ለኛ፥ እኔን ለመሰላችሁ ሆዳሞች! ካአቡነ ጳውሎስ ክሕደት ሽርና መሠርይነት ገለል ያለውን ወገን ለመምታት የመምቻውን ብትር በስውር የምንቀበል ካህናት‼ እኔና እናንተ እንደተያየን የምናጭበረብረው ሕዝብ አይየን! ካየን ወዮልን‼ ከዚያም ከዚህም እያልን በመገላበጥ የሕዝቡን ገንዘብ ለመዝረፍ ይህን "ዘመነ-ቱኀን" የምንጠቀም ገለልተኞች ነን ባዮች ወዮልን!

ይህ ዘመን በጠቅላላይቱ አገራችንና ቤተ ክርስቲያናችን ቱሐን ያፈራበት ዘመን ነው:: ይህን ስል ያለምክንያት አይደለም:: የዘመናችን መንግሥት የተከበረውን የሽምግል ባሕል ሳይቀር፥ ጠንካራ መንፈስና አላማ ያለውን ወገን ሁሉ የሚያላላበት የራሱ ቀንድ አድርጎታል:: የሕዝብ መገናኛዎችን ሁሉ የወገንን ስሜትና ንብረት መምጠጫ ቀንዱ አድርጎ ተጠቅሞበታል:: ይህን ዘመን "ዘመነ-ትኃን" ብንለው የሚስማማ ይመስለኛል::

እኛም ካህናቱ ሁለት ቀንዶች የፈጠርንበት ዘመን ነው:: አንደኛው ቀንዳችን ሕዝቡ ሰላም ሳይኖረው፥ "ሰላም ለኩልክሙ" እያልን የምናስመ ስልበት ሽፍጠና ምንደኛ ባሕርያች ነው:: ሌላው ቀንዳችን ደግሞ በማነኛውም አቅጣጫ የሕዝቡን ዘዴ የሕዝቡን ስሜትና ገንዘብ የምንዘርፍበት ነው::

ሃይማኖት በተናወጠበት የሕዝቡ ሰላም በደፈረሰበት በመከራ ጊዜ ልዑለ ባሕርይ አምላክ ከሰው ገለልተኛ አይደለም:: መላእክትም ገለልተኞች አይደሉም:: የመነኑ የገዳም ሰዎችም ገለልተኞች አይደሉም:: በዋሻ ዘግተው የሚኖሩትንም ባሕታውያን ከሰው የሚአገናኛቸው ከወገን የሚቀላቅላቸው የመከራ ዘመን ነው:: የፈጣሪና የተፈጥሮ ሕግ ይህ ሆኖ ሳለ፥ ምድር ያፈራቸውን ሁሉ የምግብ አይነት በመሻማት ላይ እያለን በመከራ ጊዜ ከሕዝቡ ገለልተኞች ነን ማለት እራስን ከተፈጥሮ ውጭ ማድረግ ነው::ምንኛ ታላቅ ወዮታ ነው!

እግዚአብሔር ከዚህ ይሰውረን!

"በዘጠኝ መለኮት" ርእስ በማቀርባት ጦማር እንገናኝ::

*ለሌሎች የቂሲስ አስተራየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለውን ደህረ-ገጽ ይመልከቱ፥*
***http://www.medhanialemeotcks.org/***